2X21 =42

07/4/03

2 ፖፖ X21

42

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አ.አ. የንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
Ethiopian Revenues and Customs Authority
A.A Commercial goods facilitation
Branch Office

ለህግ ማስከበር የሥራ ሂደት

ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት

ለደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት

ለሀብት አስተዳደር የሥራ ሂደት

አ.አ. ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

ከዋናው መ/ቤት ከዋና ዳይሬክተር በቁጥር 1.0/79/6 በ01/04/2003 በተፃፈ ደብዳቤ ለመረጃ አቅራቢዎች ሽልማት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 49/2003 እና ሕገወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ላይ ስለሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተመለከተ የወጡትን ሁለት መመሪያዎች 20 ገፅ ለአፈፃፀም የተላከ መሆኑን እያሳወቅሁ በመመሪያዎቹ መሠረት ተፈጻሚ እንዲደረግ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ፋሲል ታደሰ
ሥራ አስኪያጅ

ግልባጭ፣

- ለሥነ ምግባር ቡድን
  አ.አ. ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

40

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref.No. 1.0/78/6
ቀን / Date 01 ታህሳስ 2003

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ፤</u>

ለመረጃ አቅራቢዎች ሽልማት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 49/2003 እና ሕገወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ላይ ስለሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 50/2003 ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

መላኩ ፈንታ
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-

- ለኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ እና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለኦፐሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለለውጥ ትግበራና ደጋፊ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>



ስልክ / Tel 011-466 74 55
ፋክስ / Fax 011-466 82 44
ኢሜል / E-mail erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website WWW.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

ለአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ለምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
ለምሥራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
አዳማ

ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ባህርዳር

ለጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ጅጅጋ

ለድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ድሬዳዋ

ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
መቀሌ

ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ኮምቦልቻ

# ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣ መመሪያ ቁጥር 50/2003

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ኅዳር 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣ መመሪያ ቁጥር 50/2003

ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን ሕገ ወጥ እቃዎች በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ በጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ሊወሰድ የሚገባውን አስተዳደራዊ እርምጃ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የማጓጓዣ ባለቤቶች በንብረታቸው አማካኝነት የጉምሩክ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ የመከላከል ተግባራቸውን በተገቢው እንዲወጡ ማድረግ በማስፈለጉ እና ለሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ በንብረታቸው ላይ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል ወጥነት ያለው መስፈርት ማውጣት እና ለጉዳዮች በአፋጣኝ እልባት መስጠት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣ መመሪየ ቁጥር 50/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

አገባባቸው ሌላ ትርጉም ካላሰጣቸው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚከተሉት ቃላት እና ሀረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

1) "ሕገ ወጥ እቃ" ማለት የጉምሩክ አዋጅን ወይም ጉምሩክ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ሕጎች በመተላለፍ ወደ አገር የገባ ወይም ከአገር የሚወጣ የሚያገ[illegible] የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት እቃ ነ[illegible]

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopian Revenues and Customs Authority

2) “ባለቤት” ማለት በሕግ መሠረት ማጓጓዣውን የመሸጥ የመለወጥ ወይም በማጓጓዣው የባለቤትነት መብት ያለው ሰው ሲሆን የጋራ ባለሀብትንም ይጨምራል።

3) “የመንግስት መ/ቤት” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊልበመንግስት በጀት የሚተዳደር የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን የመንግስት የልማት ድርጅትን አይጨምርም።

4) “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው።

5) “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

6) ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/01 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ሕገ ወጥ እቃ በማጓጓዣቸው ላይ ተጭኖ በተገኘ እና በወንጀሉ ተሣትፎ በሌላቸው የማጓጓዣ ባለቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የወንጀል ተሳትፎን የማጣራት እና የመወሰን ኃላፊነት</u>

4. <u>የምርመራ ቡድን የማጣራት ኃላፊነት</u>

1. የማጓጓዣው ባለቤት በወንጀሉ ተሣትፎ እንደሌለው በራሱ የማረጋገጥ ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርመራ ቡድኑ ሕገ ወጥ እቃ በማጓጓዝ የተጠረጠሩና የተያዙ ማጓጓዣዎችን ጉዳይ ማጣራት አለበት። በማጣራት ሂደቱም የማጓጓዣው ባለቤት የወንጀል ተሣትፎ እንደሌለው ካረጋገጠ ጉዳዩ በዚህ መመሪያ የሚታይ መሆኑን የመወሰን ኃላፊነት አለበት። በዋናነት፡-

ሀ/ አጓጓዡ ወይም አሽከርካሪው የማጓጓዣው ባለቤት ያለመሆኑን፣

ለ/ የማጓጓዣው ባለቤት በማጓጓዣው ውስጥ ያልነበረ መሆ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority



45

ሐ/ ባለቤቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፈፀመው ወንጀል ተሳታፊ ወይም የወንጀሉ ፍሬ ተጠቃሚ ያለመሆኑን፣

መ/ ማጓጓዣው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመበት ወይም በቀረጥ ነፃ ያልገባ መሆኑን እና/ወይም

ሠ/ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ፈቃድ ውጪ በማጓጓዣው ላይ ለእቃ መደበቂያ ወይም ማስቀመጫ ወይም ሻግ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልተሰራለት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. የምርመራ ቡድኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4/1/ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ እንኳን መኖሩን እንዳረጋገጠ ባለቤቱ በወንጀሉ ተሳትፎ አለው በማለት የምርመራ መዝገቡን በማደራጀት ለዐቃቤ ሕግ ያስተላልፋል፣ ማጓጓዣውም በኤግዚቪትነት እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

## 5. ማጓጓዣ የመልቀቅ ውሳኔ

1. ቡድኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4/1/ የተገለፁት ሁኔታዎች አንዳቸውም ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ የማጓጓዣው ባለቤት በኃላፊነት የሚቀጣውን የገንዘብ መጠን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 ወይም 7 መሠረት በመወሰን ሰነዱን ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

2. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት በምርመራ ቡድኑ ውሣኔ መሠረት የቅጣት ገንዘቡ መከፈሉን በማረጋገጥና የተከፈለበትን ሰነድ ቀሪ በመያዝ ማጓጓዣው ለባለቤቱ እንዲለቀቅ ያደርጋል፣ ይህንንም ለምርመራ ቡድኑ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3. የምርመራ ቡድኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የተስተናገዱ እና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮችን በተመለከተ መዝገብ ያደራጃል፣ በየወሩ ለኢንተለጀንስ ምርመራና ሥጋት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት እና ለዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ይልካል፡፡

## የገንዘብ ቅጣት አወሳሰንና መጠን

### 6. የገንዘብ ቅጣት እና አወሳሰኑ

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ በተያዘው ሕገ ወጥ እቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ፤

   ሀ/ እስከ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) የሆነ እንደሆነ ቅጣት ብር 10,000 /ብር አስር ሺ/

   ለ/ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺ አንድ) እስከ 100,000 (አንድ መቶ ሺ) የሆነ እንደሆነ ቅጣት ብር 20,000 /ብር ሃያ ሺ/

   ሐ/ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺ አንድ ብር) እስከ 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) የሆነ እንደሆነ ቅጣት ብር 30,000 /ብር ሰላሳ ሺ/

   መ/ ከብር 150,001 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺ አንድ ብር/ እስከ 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ የሆነ እንደሆነ ቅጣት ብር 40,000 /ብር አርባ ሺ/

   ሠ/ ከብር 200,000/ሁለት መቶ ሺ ብር/ በላይ የሆነ እንደሆነ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ እንዲከፍል ተደርጐ ማጓጓዣው ለባለቤቱ ይመለሳል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.1 የተደነገገው ቢኖርም የተያዘው እቃ የተከለከለ ከሆነ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ ብር 50,000 በቁርጥ ተቀጥቶ ማጓጓዣው ይለቀቃል፡፡

### 7. እንስሳት፣ አነስተኛ ማጓጓዣዎች እና የሕዝብ ማመላለሻዎች

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገገው ቢኖርም የተያዘው እቃ የተጫነው፡-

   ሀ/ በአህያ ከሆነ በአንድ እንስሳ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/

   ለ/ በበቅሎ እና በፈረስ ከሆነ በአንድ እንስሳ ብር 750 /ሰባት መቶ ሃምሳ/

   ሐ/ በግመል እና በሌሎች እንስሳት ከሆነ በአንድ እንስሳ ብር 1,000 /አንድ ሺ/

   መ/ ባለ ሁለት ጐማ ሞተር ያለው ተሽከርካሪ ከሆነ ብር 3,000 /ሦስት ሺ/

   ሠ/ ባለ ሦስት ጐማ ሞተር ያለው ተሽከርካሪ ከሆነ ብር 5,000 [illegible]

2. ከ30 ሰው በላይ የሚያጓጉዝ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ከሆነ ብር 30,000፣ /ብር ሰላሳ ሺ/ በቁርጥ ተቀጥቶ ማጓጓዣው ይለቀቃል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 ወይም 7.2 የተጠቀሱት ቅጣቶች ተፈፃሚ የሚሆኑት በአንቀጽ 6.1 ወይም 6.2 የሚጣለው ቅጣት የበለጠ የሚያስቀጣ እንደሆነ ነው

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 የተመለከተው የቅጣት መነሻና ጣራ ተፈፃሚ ለማድረግ መሠረት የሚደረገው የሕገ ወጡን ዕቃ ቀረጥና ታክስ ወይም መጠኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ መቀጫው ማጓጓዣው ያወጣል ተብሎ ከሚገመተው ዋጋ ግን የበለጠ አይሆንም፡፡

## 8. ልዩ ሁኔታዎች

1. ሕገ ወጥ እቃ ሲያጓጓዝ የተያዘው ማጓጓዣ የመንግስት መሥሪያ ቤት ማጓጓዣ በሚሆንበት ጊዜ የማጓጓዣው ኃላፊ በነበረው ሰው ላይ በመስሪያ ቤቱ አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰዱ ወይም ማጓጓዣው ተሰርቆ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ይህንኑ መስሪያ ቤቱ ለባለሥልጣኑ ሲያሳውቅ ማጓጓዣው ይለቀቃል፡፡
2. ከ30 ሰው በላይ የሚያጓጉዙ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የተጓዦች የግል መገልገያ እቃ ለሆነው እና በማጓጓዣው በግልጽ ለተቀመጠ እቃ በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቅጣት በማጓጓዣው ባለቤት ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 8.2 የተደነገገው ቢኖርም በማጓጓዣው ኪስ ወይም በድብቅ ቦታ ወይም የንግድ መጠን ያለውና በግልፅ ተቀምጦ የሚታይ ሕገ ወጥ እቃ በሚገኝበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ወይም 7 የተጠቀሰው ቅጣት በማጓጓዣው ባለቤት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 9. ከወንጀል ነፃ መሰናበት

ህገወጥ ዕቃ ጭኖ የሚያዝ የማጓጓዣ ባለቤት በወንጀል ተሳትፎ አለው በሚል በፍ/ቤት ክስ ቀርቦበት በፍ/ቤት ውሳኔ በነፃ ሲሰናበት ወይም ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣቱ በገደብ ቢነሳና ማጓጓዣው ሳይወረስ ከቀረ ወይም በዚህ መመሪያ ከሚጣለው የገንዘብ ቅጣት ባነስ ከተቀጣ የማጓጓዣ ባለቤቱ በዚህ መመሪያ መሠረት መክፈል የሚገባውን የቅጣት ገንዘብ ባልተከፈለው መጠን ያህል እንዲከፍል ተደርጎ ማጓጓዣው ይለቀቃል፡፡

## 10. ተደጋጋሚ ጥፋቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት ተቀጥቶ ማጓጓዣው የተለቀቀለት የማጓጓዣ ባለቤት በድጋሚ ሕገ ወጥ እቃ በማጓጓዣው ተጭኖ ሲገኝ የአንቀጽ 5 ድንጋጌ አፈፃፀም እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ/ ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ መቀጫው በሁለት ተባዝቶ እንዲከፍል ይደረጋል፣

ለ/ ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ መቀጫው በሶስት ተባዝቶ እንዲከፍል ይደረጋል፣

ሐ/ የገንዘብ ቅጣቱ የሚባዛው በመጨረሻ በሚጣለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ነው፡፡

መ/ ለአራተኛ ጊዜ በሆነ ጊዜ የምርመራ መዝገብ ተጣርቶ ለዐቃቤ ሕግ ይላካል፡፡

## 11. ቅሬታ የማቅረብ መብት

የማጓጓዣ ባለቤት በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰነበት ቅጣት አግባብነት ላይ ቅሬታ ካለው ለባለሥልጣኑ የጉምሩክ ጉዳዮች ቅሬታ ሰሚ ቡድን ማቅረብ ይችላል፡፡

## 12. ቅጣትን ስለማስፈፀም

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጣለውን የገንዘብ ቅጣት የማጓጓዣ ባለቤቱ ማስጠንቀቂያ ደርሶት ባልከፈለ ጊዜ የተያዘው ማጓጓዣ በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 31 መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡
2. የማስጠንቀቂያው ይዘት የማጓጓዣው ባለቤት እንዲከፍል የተወሰነበትን የገንዘብ ቅጣት መጠን የሚገልጽና፣ እስከመቼ ቅጣቱ ካልተከፈለ ማጓጓዣው እንደሚሸጥ የሚገልጽ ሲሆን የማስጠንቀቂያ አሰጣጡ ሕግ በሚፈቅደው አግባብ ሆኖ ለባለንብረቱ በግንባር እንዲሰጠው ወይም በአድራሻው እንዲደርሰው በማድረግ ወይም በጣቢያው ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ መደበኛ የማስታወቂያ ሰሌዳ እንዲለጠፍ በማድረግ እንደነገሩ ሁኔታ ሊፈፀም ይችላል፡፡

## 13. ሪፖርት ስለማቅረብ

የምርመራ ቡድን በዚህ መመሪያ መሠረት የተስተናገዱና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮችን መመዝገቢያ መዝገብ ያደራጃል፣ በየወሩ ለኢንተለጀንስ ምርመራና ሥጋት ሥራ አመራር ሥራ ሂደት ወይም ለሚመለከተው ሌላ የሥራ ክፍል እና ለዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ይልካል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopian Revenues and Customs Authority



49

14. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ በአንጥልጥል የሚገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ሊስናገዱ ይችላሉ፡፡

15. <u>የተሻረ ሐግ</u>

ሕገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ የማጓጓገና ባለቤቶች ላይ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ወጥቶ የነበረው የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2001 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

16. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ------- ቀን 2003 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር